# ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፐረስ 12/16/2020:  ለዓመቱ ምርጥ አስተማሪነት እጩዎችን  ይጠቁሙ!

**የዚህ ሳምንት ዋና ርእሶች**

- ኮንከረንት የማስተማር ሂደት ምንድን ነው ለእርስዎ ምን ማለት ነው?
-  ደህንነቱ የተጠበቀ የበዓል ጉዞ መመሪያዎች
- የዓመቱ ምርጥ አስተማሪነት እጩዎችን  ይጠቁሙ!
- የዓመቱ ምርጥ የድጋፍ ሰራተኛ እጩዎችን  ይጠቁሙ!
- የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያ ይከታተሉ - የመገናኛ መረጃ ወቅታዊ ያድርጉ።
- የአእምሮ ጤንነት የበዓል ግዜ ድጋፍ ማግኛዎች
- ወጣት አንባቢያን ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. - ቲቪ ይፈለገሉ።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከVDOE በሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ ተጠቃሚ ይሆናል።
- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች ምዘገባ መረጃ ለ2020-21
- የምግብ አቀርቦት - የማከፋፈያ የግዜ ሰሌዳ እና የክረምት እረፍት ምግብ አቅርቦት

የተከበራችሁ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባላት፣

የክረምት እረፍት ከመጀመሩ በፊት በዚህ የመጨረሻ እትም  እና የ2020 ዓመት የመጨረሻው እትም  መግለፅ የምፈልገው ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቤተሰቦች በሙሉ  የደስታ፣ የሰላም እና የጢና በዓል እንዲሆን እመኛለሁ።

በሌላ ቦታ ለሚጎዙ እባካችሁን አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ እና የኮቪድ-19 መስፋፋት ለመግታት የእርስዎን ድርሻ ይወጡ። እባክዎን ያስታውሱ ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት የተሰጠው መመሪያ በቤታችን እንድንቆይ እና በርቀት የቨርችዋል ግንኙነት እንድናደርግ ይመከራል።  የሚጎዙ ከሆነ እባክዎን  ሲንቀሳቀሱ እነዚህን መመሪያዎች እና ሃሳብዎች ከግንዛቤ ያስገቡ። City of Alexandria and the Alexandria Health Department. ከክረምት የእረፍት ግዜ ስንመለስ ተማሪዎቻችን በጃንዋሪ 19፣2021 ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የተዘጋጀውን የግዜ ሰሌዳ ፕሮግራሙን  በስራ ለማዋል ዝግጁ ነን።  ይህም የሚወሰነው በዋነኛነትበከተማው የአካባቢ የኮሚይኒቲ የጤና ሁኔታ መለኪያ መሰረት ይወሰናል።  በዚህ ላይ እያንዳንዳችን የራሳችን ድርሻ ይኖረናል፤

ወደ ትምህርት ቤት መመለስን በሚመለከት እኔ ሁላችንም እንድንረዳ የምንፈልገው ነገር የኮንከረንት ( concurrent) የማስተማር አሰራር ምን  እንደሆነና ምን እንደሚመስል እንዲረዱ ነው።  የኮንከረንት (concurrent) የማስተማር አሰራር የእኛ ተማሪዎች አሁን ያላቸው አስተማሪዎች ጋር እንዲቆዩ እና  ወድ ድብልቅ (ሐይብሪድ) የሽግግር ወቅት የቨርችዋል የግዜ ሰሌዳ እንደነበረው እንዲቀጥል እድል ይሰጣል።  የኮንከረንት (concurrent) የማስተማር አሰራር  አስተማሪዎች በአካል ወይም በቨርችዋል ርቀት እንዲያስተምሩ እድል  ይፈጥራል።  እንዲሁም ሰራተኞች ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የማይችሉ አስተማሪዎች ባሉበት ሆነው ተማሪዎቻችንን ማስተማር እንዲችሉ እድል ይሰጣል።  ሰኞ በዝርዝር ስለጉዳዪ ገለፃ አድርጊያለሁ።  የእኔን የቪዲዮ ይመልከቱ እና ከታች ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።

የቤተሰብ ምርጫ ቅፁን የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ  በፓወርስኩል የወላጅ መግቢያ አካውንት (አክሰስ) አማካኝነት ይሙሉ ። እስከ አርብ ዲሴምበር 18 ድረስ መሙላት ይችላሉ።   በጃንዋሪ ወር ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ እቅዳችንን  የበለጠ ለማሻሻል ይህ በጣም ወሳኝ የሆነ መረጃ ነው ።

እንደሚያውቁት በዚህ የወረርሽኝ ወቅት የተማሪዎቻችን የማህበራዊ፣ የስሜት  እና የአካዳሚ ፍላጎቶችን የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የእኛ ሰራተኞች  ብዙ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።  ላሳዩት  ከባድ፣ ያልተቆረጠ ጥረት እና ቁርጠኝነት ባለውለታዎች ነን።

ዛሬ እኔ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ እና የደጋፍ ሰጪ ሰራተኞች  ተሸላሚ እጪዋችን እንዲመርጡ እጠይቃለሁ ፡፡ የአስተማሪዋች ተሸላሚ   የዋሽንግተን ፓስት ጋዜጣ የዓመቱ ምርጥ አስተማሪዋች ለትልቁ ሽልማትውድድር የእኛ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እጩ በመሆን ይቀርባል /ትቀርባለች።

በመጨረሻም የበዓል ግዜ  በተለይም በዚህ ባልተለመደ ወቅት የአእምሮ ሁኔታ የማባባስ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።  እርስዎ ወይም እርስዎ የሚያውቆቸው ሰዋች በመጪዋቹ ሳምንታት ድጋፍ የሚያስፈልጎቸው ከሆነና ይህን አገልግሎት ለማግኘት የሚጠቀሙ መረጃዋችን  እንዲያውቁት እንፈልጋለን።  ከዚህ በታች የቀረቡትን የአእምሮ  ጤና ድጋፎች ይመልከቱ።

እባካችሁ እራሳችሁን፣ ጤንነታችሁን ጠብቁ እና ተሳታፊ ይሁኑ። በ2021 ለመገናኘት ያብቃን!

ዶ/ር ግሪጎሪ  ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr).

## ኮንከረንት የማስተማር ሂደት ምንድን ነው ለእርስዎ ምን ማለት ነው?

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ወደ ትምህርት ቤት በጃንዋሪ በሚመለስበት ወቅት “ኮንከረንት የማስተማር ሂደት” ይገለገላል ፡፡

እባክዎን ኮንከረንት የማስተማር ሂደት ምንነት በተመለከተ እና ለእርስዎ ምን ጠቀሚታ እንዳለው እና የቤተሰብ ምርጭ ቅፁን እስከ ዲሴምበር 18 ድረስ እንዴት እንደሚሞሉ ከዶ/ር ግሪጎሪ  ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr). የተላከ መልእክት ይመልከቱ ፡፡




(Watch in English, Spanish, አማርኛ or Arabic.)

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፤ የቤተሰብ ምርጭ ቅፁ እና መልሶችን ይመልከቱ እንዲሁም  ስለ ኮንከረንት የማስተማር ሂደት ምንነት በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዋች ይመልከቱ።

## ደህንነቱ የተጠበቀ የበዓል ጉዞ መመሪያዎች

የእኛ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንዲችሉ እድሉን ለማመቻቸት  እርስዎ የሚያግዙበት እንደኛው መንገድ በበዓሉ ወቅት የእርስዎን ጎዞ የተገደበ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡  የእኛ  ትምህርት ቤቶች የመክፈት ሁኔታ በኮሚዩኒቲው የጤንነት ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡  እርስዎ ጉዞ የሚያደርጉ ከሆነ እባክዎን ማድረግ የሚችሉትን ጥንቃቄ ሁሉ ያድርጉ እና ወደ አሌክሳንደሪያ ሲመለሱ ራሶዋን በማግለል (ኮራንታይን) በማድረግ ይቆዩ፡፡

የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት አጥብቆ የሚያሳስበው ጉዳይ ኖሪዎች በአካል ከመገናኘት ይልቅ በርቀት ቨርችዋል ግንኙነት [virtual gatherings] እንዲያደርጉ  እና ጉዞ እንዳይኖር ማድረግ ፤  ከቅርብ ቤተሰብ ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት መቀነስ ነው፡፡




## የዓመቱ ምርጥ አስተማሪነት እጩዎችን  ይጠቁሙ!

በዚህ ዓመት ምንም እንኳን በጣም ፈታኝ በሆነ ማንም ሰው ከሚገምተው በላይ ቢኖርም ከምንግዜውም በበለጠ የእኛ አስተማሪዎች ተማሪዎቹን እና ቤተሰቦችን   ለማገልገል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ፡፡  በየክፍሉ ያሉ አስተማሪዎች  አዳዲስ እውቀቶችን ተምረዋል እና ቴክኒዋሎጂ ከመለማመድ በተጨማሪ የርቀት ቨርችዋል የማስተማር አሰራር ችግር ለመቆቆም ችለዋል፡፡  ሁሉም አድናቆት  እና ምስጋና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ከተገቢ ከመደበኛ ስራ ባላፈ ከፍተኛ ስራ ያከናወነ አስተማሪ የሚያውቁ ከሆነ እባክዎን ስሙን/ስሞን በእጩነት ያስተላለፉ ለዓመቱ ምርጥ አስተማሪ ውድድር።

**የአስተማሪ እጩ ለመምረጥ የፅሁፍ ድጋፍ ደብዳቤ እስከ ጃንዋሪ 7 ቀን 4.00 ከሰዓት በኋላ ድረስ [ለርእስ መምህራኑ ኢሜል ያድርጉ]() ይላኩ።** ፅሁፉን ለማዘጋጀት መስፈርቱን ከታች ይመልከቱ።

**የአስተማሪ እጩ ተወዳዳሪ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሙላት ይኖርበታል ።**

- በተማሪዎች ላይ የመማር ፍላጎት እና ውጤታማ የመሆን ፍላጎት እንዲኖራቸው ማስቻል።
- የተማሪዎችን የግል ፍላጎት መረዳት፣ ያላቸውን ችሎታ እንዲያሳድጉ ማበረታታት እና የራሳቸው የመተማመን ሁኔታ እንዲያሳድጉ ማድረግ።
- የትምህርት ዘርፉን በሚገባ ማወቅ እና ለተማሪዎች ጋር በሚገባ የማሳወቅ ችሎታ መኖር።
- ከጎደኞቻቸው እና የኮሚዩኒቲ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ማስቻል።
- አግባባነት ያለው የአመራር ችሎታ ማሳየት።
- በ2020-21 የትምህርት ዓመት የአስተማሪነት ስራቸው ላይ የቆዩ።

በጃንዋሪ እያንዳንዱ ርእሰ መምህር የየትምህርት ቤቶቻቸውን የምርጥ አስተማሪዎች ይመርጣሉ። ከዚያም የአጠቃላይ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ምርጥ አስተማሪዎች እጩ በመሆን ይቀርባሉ። የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ፓናል የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የዓመቱን ምርጥ አስተማሪ ይመርጣል ። የዋሽንግተን ፓስት ጋዜጣ የዓመቱ ምርጥ አስተማሪዎች ለትልቁ ሽልማት ውድድር የእኛ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እጩ በመሆን ይቀርባል /ትቀርባለች። አሸናፊ ከዋሽንግተን ፓስት ጋዜጣ የዓመቱ ምርጥ አስተማሪዎች ጋር አብሮ በኤፕሪል ወር ይገለፃል።

## የዓመቱ ምርጥ የድጋፍ ሰራተኛ እጩዎችን ይጠቁሙ!

የእኛ የትምህርት ቤት ዲቪዝን ዋና የልብ ትርታ የሆኑትን ዓርዓያ የሚሆኑ ሰራተኞች ለማክበር ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከመደበኛ ሰራው ኋላፊነት ባለፈ ስራቸው የሚያከናውኑ ምርጥ የዓመቱ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ለመምረጥ ጥቆማ እንዲያደርጉ ለእርስዎ ጥያቄ ያቀርባል ። ትምህርት ቤቶቻችን ውጤታማ እንዲሆኑ እና ለተማሪዎቻችን ደህንነት ሲባል ትልቅ ችሎታ ያላቸውን ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መኖር በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

የእኛ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የቢሮ ሰራተኞች፣ የምግብ ቤት ሰራተኞች ፣ መለስተኛ ባለሞያዎች የትምህርት ቤቱ ነርስ፤ የቤተመፅሃፍት ባለሞያዎች እና ሌሎች በርካታ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ያካትታል። የማስተማሪያ ፍቃድ የሌላቸው ዳይሬክተር እና አስተዳደሪ ያልሆኑት ሰራተኖች ናቸው።

እርስዎ ለመምረጥ የሚያስቡት ሰው መስፈርቱን የሚያሞላ / የምታሞላ ስለመሆኑ እርግጠኛ አይደሉም? ኢሜል አድርጉልን [news@acps.k12.va.us](mailto:news@acps.k12.va.us).

**የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ እጩ ለመምረጥ ለመጠቆም የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛውን የሚመለከት የድጋፍ ደብዳቤ እስከ ጃንዋሪ 7 ከቀኑ 4.00 ሰዓት ድረስ [ለት/ቤቱ ርእሰ መምህር]() ወይም [ለዲፓርትሜነት ዳይሬክተር]() ኢሜል ያድርጉ።**

በጃንዋሪ እያንዳንዱ ርእሰ መምህር የየትምህርት ቤቶቻቸውን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ይመርጣሉ። ከዚያም የአጠቃላይ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ምርጥ አስተማሪዎች እጩ በመሆን ይቀርባሉ። የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ፓናል የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የዓመቱን ምርጥ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ይመርጣል ። የእኛ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አሸናፊ የሚሆነው በኤፕሪል ወር ይገለፃል።

## የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያ ይከታተሉ - የመገናኛ መረጃ ወቅታዊ ያድርጉ።

የዛሬውን የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያ ደርስዎታል? እባክዎን ወቅታዊ የአየር ንብረት ማስጠንቀቂያ፤ መረጃ ዋች በቴክስት እና በኢሜል እንዲደርስዎ ለማድረግ  እንዲቻል ለ school registrar ወቅታዊ የሞባይል ስልክ፤ ኢሜል አድራሻ ለት/ቤት ሪጅስትራር ይሰጡ ፡፡ መረጃዋች ወደእርስዎ እንዲደርስዎ ለማድረግ እንድንችል  መረጃውን ወቅታዊ የማድረጊያ ግዜው አሁን ነው።

ሁሉንም የትምህርት ቤት ህንፃዋች መዝጋት የሚያስፈልግ ከሆነ  በኤሌትሪክ መጥፋት ምክንያት ወይም በመጥፎ አየርንብረት  ምክንያት ምንም የምግብ ክፍፍል ፣ ከእኛ ወደ ውጭ የሚንቀሳቀስ ትራንስፓርት አይኖርም፣ ወይም የቨርችዋል ፕለስ+ የልጆች ጥበቃ አገልግሎት በዚያ ቀን አይኖርም ፡፡

የእኛ የአየር ንብረት ሁኔታ ማሳወቂያ በሚከተሉትን መንገዶች በአራት ቋንቋዋች ይገለፃል ፤

- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ድረገፅ፤ ( መረጃዋች በቅድሚያ በዚህ ነው የሚወጡት።)
- የቴክስት መልእክት እና ኢሜል ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ወላጆች/አሳዳጊዋች።
- ኤስ  ፌስ ቡክ፤ Facebook እና ቲዊተር Twitter
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሞባይል አፕልኬሽን
- ACPS-TV የከተማው ኬብል ቻናል  71
- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የአደጋ ጊዜ መገናኛ፤ 703-866-5300
- የየአካባቢው የከተማ ሬዲዮ እና ቴሌቭዝን፤
- የአሌክሳንደሪያ ከተማ ኢዜና — ይህን አገልግሎት የኮሚዮኒቲ አባል እና ሰራተኛችም ለማግኘት እንዲመዘገቡ እናበረታታለን።

## የአእምሮ ጤንነት የበዓል ግዜ ድጋፍ ማግኛዋች

ተማሪዋች ወይም ሰራተኞች የማህበራዊ ፣ የስሜት ወይም የአእምሮ ጤና ድጋፍ የሚፈልጉ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ለክረምት ዝግ ሲሆን እነዚህ አማራጭ አገልግሎት መስጫዋችን ማግኘት ይችላሉ።

- ችግር ሲከሰት ፣ Crisis Text and Crisis Link:
  - ቴክስት፤ CONNECT to 85511
  - ይደውሉ፤ 703-527-4077
- Alexandria Safe Place
- Alexandria City 24-Hour Emergency Mental Health Services
- የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርትሜንት እና  ጤና ዲፓርትሜንት መገናኛ
- Inova Alexandria Hospital (ER)

መረጃው በተጨማሪ በዚህ ላይ ይገኛል ፤ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የቨርችዋል ፕለስ + የአእምሮ ጤና ድረገፅ።

## ወጣት አንባቢያን ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. - ቲቪ ይፈለጋሉ።

ሁሉም የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎች ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. - ቲቪ በከተማው ኬብል ቻናል 71 የሚተላለፍ ጮክ ብሎ በማንበብ የተቀረፀ ቪዲዮ እንዲያቀርቡ ጥያቄ እናቀርባለን። የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የልጆች የንባብ ፕሮግራም አማካኝነት ተማሪዎች በራሳቸው ሲያነቡ የተቀረፀ እድል ያገኛሉ ከተመረጡ መፅሀፊት ሕትመቶች እና የተቀረፁት ቪዲዬዎችን ለሌሎች ተማሪዎች ለማጋራት ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሐሙስ፣ ዲሴምበር 17 ቀን ከሰዓት በኋላ !በዙም ከእኛ ጋር ይሁኑ. ። የመግቢያ ኮድ፤ read123

## የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከVDOE የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ ተጠቃሚ ይሆናል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከቨርጂኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት ተጨማሪ የደህንነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ግዢ የሚውል $250,000 የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ችሎል ።

የገንብዘብ ድጋፉ የሚውለው ለኮራ ኬሊ አንደኛ ደረጃ የሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኒዋሎጂ ት/ቤት፣ ጆርጅ ዋሽንግተን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ማቲው ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና ለቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው።

የተሰጠው የገንዘብ ድጋፍ የቪዲዬ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ለመግዛት እና የቪዲዬ የውስጥ የመገናኛ መስመር ለመዘርጋት፣ የት/ቤት አውቶብስ የውስጥ ካሜራ ፣ የመገናኛ ብዙሃን ማሳሪያዎች ፣ የጎብኝዋች መለያ መሳሪያ ፣ የውጭ መግቢያና መውጫ መቆጣጠሪያ መሳሪያ፣ ባለሁለት መንገድ መገናኛ ሬዲዬ፣ የሴክዊሪቲ ማሳሪያ እና ሌሎች የደህንነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ግዢ ላይ ይወላል።

“”በዚህ ዓመት የቨርጅኒያ ት/ቤቶች ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና ሰራተኞችን ደህንነት በመጠበቅ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የምንሰጠውን ድጋፍ እጥፍ አድርገናል” ብለዋል አገረ ግዢው Governor Ralph Northam ። “ ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን የወረርሽኝ ሁኔታ እንዴት ሊያልፉ እንደሚችሉ ድጋፍ በማድረግ ላይ አትኩሮት አድርገናል እና በአካል በመገኘት ትምህርት ለመከታተል ዝግጁ እንዲሆኑ አገዛ እያደረግን ነው ። ይህም ሁሉንም ሰው ደህነት ለማስጠበቅ እና ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ድጋፍ ለማድረግ ትምህርት ቤቶቻችን አስፈላጊው የደህንነት መቆጣጣሪያ መሳሪያዎች ፣ እቃዎች እና አሰራር ማድረግ ነው። ”

በድምሩ $12 ሚሊዬን በስቴቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች የደህንነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ የገንዘብ ድጋፍ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎችና ጎብኝዎችን የሚያገለግል ለ489 ት/ቤቶች በመላው ቨርጅኒያ ያሉ በ102 የት/ቤት አስተዳደር ክልል ውስጥ እንዲከፋፈል ተደርጓል።

## የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች ምዘገባ መረጃ ለ2020-21

በፎል ወቅት ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እስከ ፎል ወቅት ያሉ የተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ የተማሪዎች ቁጥር መረጃ ሪፓርት ለቨርጅኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት እንዲያዘጋጅ ይጠየቃል። በዚህ ዓመት ሪፓርቱ ለአሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ ኖቬምበር 12፣ 2020 ቀርቦል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪ ለ2020-21 የትምህርት ዘመን የቅድመ ምደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 15,588 ነበር። በትምምህርት ቤት አስተዳደሩ የተማሪዎች ቁጥር ብዛት በግምት ወደ 500 ቀንሶል ከሰኔ 2020 ። ይህም በተለይ በአንደኛ ደረጃ ት /ቤት ከፍተኛ መቀነስ ይታያል።

ስለተማሪዎች ብዛት ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ይህን ይመልከቱ። ACPS Fast Facts.

# የምግብ አቀርቦት - የማከፋፈያ የግዜ ሰሌዳ እና የክረምት እረፍት ምግብ አቅርቦት

የክረምት እረፍት ከመጀመሩ በፊት የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የምግብ አቅርቦት የመጨረሻው ቀን  አርብ ፣ ዲሴምበር 18 ነው።  የምግብ ክፍፍሉ ተመልሶ የሚጀምረው  ሰኞ፣ ጃንዋሪ 4፣ 2021 ይሆናል።

የክረምት እረፍት ግዜ የ5 ቀናት የልጆች ምግብ አቅርቦት ጥያቄ  ላቀረቡ ምግቡ  በትምህርት ቤት ድረገፅ በመረጡት ስፍራ ሐሙስ፣ ዲሴምበር 17 ከጥዋት 7.30 እስከ እኩለ ቀን ድረስ ያካሄዳል።  በዲሴምበር 17 ያልተወሰደ የልጆች ምግብ ከዚያ በኋላ ለመውሰድ አይቻልም - ምንም ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም።  ይህን ሁኔታ የሚያስተጎጎል ሁኔታ ከተፈጠረ ወቅታዊ መልክት እንልካለን።

**ALIVE የክረምት እረፍት ወቅት የተማሪዋች የቁርስና የምሳ የታሸገ ምግብ አቅርቦት ፤**

ሰኞ፣ ዲሴምበር 28 ቀን ከጥዋት 8.30 እስከ 10.30 ድረስ ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዋች በዊሊያም ራምሴ እና በቺክ አርምስትሮንግ የመዝናኛ ማእከል ALIVE የሰባት ቀናት ምግብ ያከፋፍላል።   እያንዳንዱ ተማሪ አንድ የታሸገ ምግብ ማግኘት ይችላሉ።

---

ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዋችና እድሚያቸው ከሁለት አመት በላይ ለሆኑ ልጆች  የምግብ አቅርቦት ብዙ የማከፋፈያ ቦታዋች በመላው አሌክሳንደሪያ ከተማ አሉት።  የምግብ ማከፋፈያ ቦታዋች የሚያሳየው ክካርታ ይመልከቱ .

**ይዞ-መሄድ የምግብ ማከፋፈያ ቦታዋች፡**

ይዞ-መሄድ ቁርስ፣ ምሣ እና መክሰስ (ስናክ) ምግቦች ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ከጥዋት 7.30 እስከ ከቀኑ 12.00 ድረስ በሚከተሉት ቦታዋች ይሰጣል፤

- **ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት**
  5700 Sanger Avenue  Alexandria, VA 22311
- **የፍራንሲስ ሲ ሐመንድ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**
  4646 Seminary Road, Alexandria, VA 22304
- **ኮራ ኬሊ አንደኛ ደረጃ የሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኒዋሎጂ ት/ቤት፤**
  3600 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305
- ጀፈርሰን ሁዊስተን ቅደመ-መደበኛ - 8ኛ IB ትምህርት ቤት
  1501 Cameron Street, Alexandria, VA 22314
- **ማውንት ቨርነን የኮሚዩኒቲ ት/ቤት**
  2601 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305
- **ፓትሪክ ሔንሪ K-8 ት/ቤት**
  4643 Taney Avenue, Alexandria, VA 22304
- **የቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
  3330 King Street Alexandria, VA 22304

እንዲሁም ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት በ “ተንቀሳቃሽ - ፓፕ አፕ” የማከፋፈያ ቦታዋች የሚገኙበት ቦታዋች፤

- **ሜሶን አፓርትሜንት (Mason Apartments)  በ South Reynolds Street Alexandria, VA 22304**10:45 እስከ 11:15 ድረስ  ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት ፡፡
- **ብረንት ፕሌስ አፓርትሜንት (Brent Place Apartments)  በ 375 South Reynolds Street, Alexandria, VA 22304**  11:20- 11:50 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ
- **ሩቢ ተከር የቤተሰብ ማእከል (Ruby Tucker Family Center) በ 322 Tancil Court,  Alexandria**, VA 22314 10:45 - 11:15 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ
- **ኮሚዮኒቲ ሎጂንግ (Community Lodgings) በ 607 Notabene Drive, Alexandria, VA 22305**  ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ  ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ፡፡
- **አልድ ታወኔ ዌስት አፓርትሜንት (Old Towne West Apartments)**  (የመኪና ማቆሚያ ቦታ) በ 500 South Alfred Street, Alexandria, VA 22314
  ጥዋት 11:20 - 11:50ድረስ  ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ፡፡
- **ፍሎረንስ ድራይቭ እና ፎር ማይል መገናኛ መንገድ(Florence Drive እና Four Mile Road**) **Alexandria, VA 22305** ከጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ  ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት፡፡
- **ዘ ፊልድስ** (**The Fields) በ 4309 Duke Street, Alexandria, VA 22304** ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ  ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ፡፡
- **በቤንጊተን ክሮኒሲንግ (Bennington Crossing) አፓርትሜንት በ 441 North Armistead Street, Alexandria, VA 22312**  ጥዋት 11:30 እስከ እኩለቀን ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት ፡፡
- **(**ከባንክ ኦፍ አሜሪካ ጀርባ) **2727 Duke Street , Alexandria, VA 22314**   10:45 እስከ 11:15 ጥዎት

**ምግብ ለማግኘት ምዝገባም ሆነ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡**

**<u>ማስታወሻ፤</u> ማክሰኞ እና ሐሙስ ምንም የምግብ ክፍፍል አይኖርም፡፡** የተወሰኑ ቀናት እንዲሆን መደረጉ የሶሻል መራራቅን አሰራር ለመከተል እና አስፈላጊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን ለመቀነስ ነው፡፡ ለሁለት ቀናት የሚሆን ምግብ ሰኞ እና እሮብ ቀናት ይከፋፈላል እንዲሁም አርብ ለሶስት ቀናት የሚሆን ምግብ  ይሰጣል፡፡

**የአሌክሳንደሪያ ከተማ  ሌሎች የምግብ አቅርቦት ምንጮች**

በአሌክሳንደሪያ ከተማ የምግብ ማቅረቢያ በታዋች እና ሰዓት የጊዜ ሰሌዳ  ለማወቅ ይህን ይመልከቱ፡፡
www.hungerfreealexandria.com  ወይም ስልክ 703-662-1067. .

**ጥያቄዋች? ወይም አስተርጎሚ ይፈልጋሉ?**

ጥያቄዎን በስፓኒሽ፣ በአረብኛ ወይም በአማርኛ ቴክስት ያድርጉ፤
- ACPSMEALS to 797979 (እንግሊዘኛ እና ስፖኒሽ፤)
- ለ703-927-6866  ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ  (በአማርኛ )
- ለ703-927-7095 ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ  (በአረብኛ )

ወይም

የኤፍ.ኤ.ሲ.ኢ.(FACE) ማእከል የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ የወላጆች የመረጃ መስመር አሁን ከሰኞ - አርብ ከጥዋት 9.00 እስከ 1.00 ቀን ድረስ ይኖራል።

- የስፓኒሽ/እንግሊዘኛ 571-775-9719 ስልክ ይደውሉ።
- የአማርኛ/እንግሊዘኛ 703-927-6866 ስልክ ይደውሉ።
- የአረብኛ/እንግሊዘኛ 703-927-7095 ስልክ ይደውሉ።

**የደህነት ማስታወሻ**

እባክዎን ያሳታውሱ በእርስዎ እና በሚቀጥለው ቤተሰብ ወይም ሰዎች መካከል በምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች ስድስት ፊት ርቀት በመጠበቅ የሶሻል ዲስታንሲንግ (ተራርቆ መቆም) አሰራር ያክብሩ።

ማንኛውም የመተንፈሻ አካላት ህመም ምልክቶች ያሉት ሰው ለምሳሌ ትኩሳት፣ አፍንጫ መዝረክረክ፣ የሚከረከር ጎሮሮ ፣ ሳል፣ ወይም የመተንፈስ ችግር የምግብ ክፍፍል በሚደረግበት ቀን ወይም ከዚያ ቀን 24 ሰዓት በፊት ከለብዋት እባካችሁ ወደ ምግብ ማከፋፈያ ቦታ አይምጡ። እና ወደ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይደውሉ። የራስዎ ሐኪም ከሌለዋት እና በክሊኒክ ያልተመዘገቡ ከሆነ የአስቸኳይ ጊዜ ህክምና ወይም የድንገተኛ ጊዜ ህክምና ቦታ ይደውሉ።

## ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ወቅታዊ መረጃ

ለማንኛውም ወቅታዊ መረጃ ይህን ይመልከቱ፤ www.alexandriava.gov/Coronavirus.

## የጤና ጉዳይ ማሳሰቢያዎች

**ጤንነት አይሰማዎትም?**

ከቤተሰብ ሀኪም ጋር ይገናኙ፤ ምንም የጤና ኢንሹራንስ የለዎትም? ከኔበርሁድ ሄልዝ(Neighborhood Health) ጋር በስልክ ይገናኙ 703-535-5568.

---

**ጥያቄዎች፣ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም አስተያየት ? ከእኛ ጋር ይገናኙ፤.**